የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር

የማህበረሰብ መር የተፋጠነ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፤ የአካባቢና የግል ንጽህና ፕሮጀክት (ኮዋሽ)



# በኮዋሽ ሴቶችን የማብቃት አተገባበር

ጥር 2011 ዓ.ም

# ስለኮዋሽ አጭር ማብራሪያ

የማህበረሰብ መር የተፋጠነ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፤ የአካባቢና የግል ንጽህና ፕሮጀክት (ኮዋሽ) በኢትዮጵያ መንግስትና በፊንላንድ መንግስት ትብብር የሚተገበር ሲሆን እስከ አሁን ሶስት የትግበራ ምዕራፎችን አካቷል፡፡ ኮዋሽ የውሃና ሳኒቴሽን ሁለገብ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ ያስቀመጠችውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካት እንዲያግዝ ሆኖ የተቀረጸ ፕሮጀክት ነው፡፡

**ምዕራፍ አንድ**
ከሐምሌ 2003 ዓ.ም እስከ መስከረም 2006 ዓ.ም

**ምዕራፍ ሁለት**
ከጥቅምት 2006 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 2008 ዓ.ም

**ምዕራፍ ሦስት**
ከነሐሴ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2012 ዓ.ም

ኮዋሽ የማህበረሰብ ትግበራ ፕሮጀክት ስልትን የሚጠቀም ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአምስት ክልሎች ማለትም በአማራ ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ በኦሮሚያ ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ እና በትግራይ ለሚገኙ 76 ወረዳዎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ከተሰማሩ ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

# የማህበረሰብ ትግበራ ፕሮጀክት ስልት

ኮዋሽ "የማህበረሰብ ትግበራ ፕሮጀክት " ስልትን የሚጠቀም ሲሆን ይህንን ስልት ልዩ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች መካከል የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡

- ህብረተሰቡን በመወከል የውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴዎች የተቋማት እቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና አስተዳደር ሃላፊነትን ይወጣሉ፡፡ ይህም የግንባታ እቃዎች ግዢንና የኮንትራት ውሎችን መፈጸም ያካትታል፡፡
- የተቀላጠፈ አሠራርን የሚተገብር ሲሆን ግልጽ የሆነ የአሠራር ቅደም ተከተልና መመሪያዎችን ይከተላል፡፡ በርካታ የአቅም ግንባታ ሥራዎችንም ያከናውናል፡፡
- በየደረጃው የማህበረሰብ ተሳትፎን በማሳደግና የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር / እንዲጎለብት በማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የውሃና ንጽህና ተቋማት ዘላቂነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡



የማህበረሰብ የውሃ ጣቢያ፣ የእጅ ፓምፕ የተገጠመለት የእጅ ጉድጓድ/ትግራይ ክልል/መላኩ ተ.

# በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ዘርፍ
# ለሴቶች ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት

በአብዛኛው የአገራችን ክፍል ውሃ መቅዳት በሴቶችና ሕጻናት ላይ የተጣለ የሥራ ኃላፊነት ነው፡፡ ውሃን በቅርብ ርቀት ላይ ያለማግኘት ተጨማሪ የሥራ ጫና የሚፈጥር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቀድተው የሚያመጡት ውሃ በቂና ጥራቱን የጠበቀ ላይሆን ይችላል፡፡

ውሃን ለማምጣት የሚያውሉትን ጊዜና ጉልበት ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን ለማከናወንና ክህሎታቸውን ለማሳደግ በሚያግዙ የአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ እንዲያውሉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

.
ውሃ ቀድተው፣ ተሸክመው፣ ረጅም ርቀት ሲጓዙ ለጤና መታወክ ችግር ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡

ሴት ተማሪዎች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ከትምህርት ገበታ ለመቅረት ይገደዳሉ፡፡

ሴቶች በወር አበባና በእርግዝና ወቅት የበለጠ ተጎጂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

በቀን ብርሃን መጸዳዳት አዳጋች በመሆኑ የሚመገቡትን ምግብና የሚጠጡትን ፈሳሽ ለመቀነስ ይገደዳሉ፡፡

የተሟላ የሳኒቴሽን አገልግሎት ያለማግኘት ሴቶችንና ልጃገረዶችን የበለጠ ተጎጂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ጨለማን ተገን አድርገው ለመጸዳዳት የሚገደዱ በመሆናቸው ለአካላዊና ጾታዊ ጥቃት ይጋለጣሉ፡



የኢትዮጵያ ሴቶች ውሃ ለመቅዳት ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች መካከል በከፊል/ ደብብሕ ክልል/ አማራ ክልል/መላኩ ተ.

# ማብቃት ስንል ምን ማለታችን ነው ?

"ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ምርጫን ለማድረግ እና እነዚህን ምርጫዎች ተግባራዊ በሆነ እንቅስቃሴ ወደሚፈለገው ውጤት መለወጥ እንዲችሉ የአቅም ማበልጸጊያ ሂደት ነው፡፡" የዓለም ባንክ

"ሴቶች አቅማቸውን ለማጎልበት፣ የራሳቸውን ህይወት በስኬት ለመምራትና ስልታዊ ምርጫዎችን የማድረግ ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል ሂደት እንደሆነ ይገልጻል፡፡"

የሥርዓተ ፆታ እኩልነት ላይ የሚሰራው የአውሮፓውያን ተቋም

"ሴቶች ለራሳቸው ያላቸው አተያይ፣ ምርጫን የማወቅ እና የመወሰን መብት፣ ለዕድሎች እና ግብዓቶች ተደራሽ የመሆን መብት፣ በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ የራሳቸውን ህይወት የመምራት ነጻነት፣ እና በብሔራዊ እና አለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ ፍትሃዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት እንዲፈጠር ለማስቻል ማህበራዊ ለውጥ የሚመራበት አቅጣጫ ላይ ተጽእኖ የማድረግ ችሎታ መሆኑን ይገልጻል፡፡" የተባበሩት መንግስታት

# ሴቶችን ለማብቃት አራቱ ቁልፍ ዘርፎች

## የአገልግሎት ተጠቃሚነት ብልጽግና

- የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
- የመጸዳጃ ቤት አቅርቦትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
- የተሟላ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
- ጥቃትን ለመቃወም/ለመታገል መቻል (የቤት ውስጥ ድብደባንና ፆታዊ ትንኮሳዎችን ይጨምራል)
- ከአደጋና ከጥቃት መጠበቅ
- የውሃ ወለድ በሽታዎች መቀነስ

## ማህበራዊና ባህላዊ ብልጽግና

- የሴቶች የመናገር መብት
- የሴቶች የመናገር ችሎታ
- የሴቶች በአደባባይ ሃሳብን የመግለጽና የመደመጥ አቅም
- በውሳኔ አሰጣጥ የላቀ ተሳትፎ መኖር
- መረጃ የማግኘት ተደራሽነት መጨመር/ማደግ
- በመረጃና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመወሰን መቻል
- የገበያ፣ የጤና አጠባበቅና የትምህርት ተደራሽነት መጨመር/ማደግ
- ከቦታ ወደ ቦታ ያለስጋት የመዘዋወር ነፃነት

## የፖለቲካ ብቃት

- ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ መሆን
- የመምረጥና የመመረጥ መብት ባለቤት መሆን
- በፖለቲካ ስብሰባዎች በንቃት ተሳታፊ መሆን
- በፖለቲካ ቅስቀሳዎች በንቃት ተሳታፊ መሆን

## የኢኮኖሚ ብልጽግና

- ገቢ በሚያስገኝ የሥራ ዘርፍ መሰማራትና የወጪ ዝርዝር የመወሰን አቅም
- በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
- ከመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን
- አስፈላጊውን ክህሎት በማዳበር በገበያ ተወዳዳሪ መሆን
- በጤና መሻሻል ምክንያት የህክምና ወጪን መቀነስ

# ሴቶችን ለማብቃት የኮዋሽ ድጋፍ ፤ 17 ነጥቦች

ስ በክልል የድጋፍ ቢሮዎች የሥርዓተ ጾታ ባለሙያ መቅጠር ወይም ሥራውን የሚከታተል ሠራተኛ መመደብ

ል የስልጠና ማኑዋሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት

ቶ መረጃዎች በፆታ የተለዩና የተተነተኑ

ች እንዲሆኑ ማድረግ

ጥሩ አፈፃፀም ለሚያሳዩ የውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴዎች የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ምሳሌ እንዲሆኑ ማስቻል

## የአገልግሎት ተጠቃሚነት ብልጽግና

የወረዳና የቀበሌ ባለሙያዎችንና አመራሮችን በማሰልጠን የማ.ፐ.ትን ማፋጠን

የድሃ ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች የውሃና ንጽህና አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ

የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ለመገንባትና ለመጠቀም እንዲቻል የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮች ላይ ሴቶችንና ወንዶችን ማካተት

የውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ቡድኖችንና የልጃገረድ ቡድኖችን በማጠናከር የት/ቤት የውሃና መጸዳጃ ተቋማት በዘላቂነት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግና የልጃገረዶችን የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤ ማሳደግ

## ማህበራዊና ባህላዊ ብልጽግና

ሥርዓተ ጾታን ለማስረጽ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለኮዋሽና ለአጋር መሥሪያ ቤት ሠራተኞች እንዲሁም ለህብረተሰቡ መስጠት

የንጹህ መጠጥ ውሃና የንጽህና አገልግሎት ፍላጎትን መፍጠር፣ በተለይም መገለል የሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ

በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ዘርፍ ሥርዓተ ጾታንና የአካል ጉዳተኞችን አካታችነት ያማከለ ጥናት ማካሄድና የጥናቱን ውጤት ተግባራዊ ለማድረግ ለአጋር ድርጅቶች ማሰራጨት

ስርዓተ ጾታን ለማስረጽ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ድርጅቶችና የልማት አጋሮች ጋር በቅንጅት መስራት፣ የመረጃ አውታር መዘርጋትና በስፋት የግንዛቤ መፍጠር ሥራዎችን መስራት

## የፖለቲካ ብቃት

የሴቶችን የተሳትፎ ድርሻ በኮታ ከመወሰን ባሻገር ሴቶችን ወደ አመራር ማምጣት

በውሃና ንጽህና ኮሚቴ ውስጥ ሴቶች የአመራር ቦታዎችን መያዝ እንዲችሉ የውሃና ንጽህና ኮሚቴ አባላት የመሪነት ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ

ለሴቶችና ሌሎች መገለል ለሚደርስባቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች (የአካል ጉዳተኞችን ጭምር) የመሰብሰቢያ ጊዜና ቦታ ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ

የውሃ አቅርቦትና ንጽህናን በተመለከተ ከሴቶችና ከወንዶች የሚገኘውን እውቀት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ

## የኢኮኖሚ ብልጽግና

ለሴቶች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በተለምዶ "የወንዶች ሥራ" ነው በሚባሉ የምርት ስራዎች ተሳታፊ ማድረግ



# ውጤትና የአፈጻጸም መለኪያዎች

**በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ሥራዎች አማካኝነት ሴቶችን ማብቃትና መሪ እንዲሆኑ ማስቻል ይረጋገጣል**

ውጤት 1፡ በኮዋሽ ወረዳዎች ውስጥ፣ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴ ውስጥ የሚገኙ የሴት አመራሮች ቁጥር ይጨምራል

ውጤት 2፡ በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ በውሃ ተቋማት ጥገና፣ በመለዋወጫ ዕቃዎች አቅርቦት፣ በሳኒቴሽን ግብይትና በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ በሴቶች የሚመራ ኢንተርፕራይዝ ይቋቋማል

ውጤት 3፡ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን እቅድና አፈጻጸም የሥርዓተ ጾታን እና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ማስረጽ እንዲቻል የአጋር ድርጅቶች አቅም ይገነባል

## የአፈጻጸም መለኪያዎች (አመላካቾች)

- ☞ ከውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴዎች መካከል 50 በመቶና ከዚያ በላይ ሴት አባላት ያሉት የውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴ ብዛት በመቶኛ
- ☞ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴዎች ውስጥ በሴቶች የተያዙ የአመራር ቦታዎች ብዛት በመቶኛ (የአመራር ቦታዎች ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፤ ሰብሳቢ፣ ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ)
- ☞ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴዎች ውስጥ ሴቶች ሦስቱንም የአመራር ቦታዎች የያዙበት የውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ኮሚቴ ብዛት በመቶኛ
- ☞ ቢያንስ 40% የሚሆኑት አባላት ሴቶች የሆኑበት በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ በሴቶች የሚመሩ ኢንተርፕራይዞች በመቶኛ
- ☞ ትርፋማ የሆኑ በሴቶች የሚመሩ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በመቶኛ
- ☞ በአቅም ግንባታ ስልጠና የተካፈሉ ሴቶች ቁጥር በመቶኛ
- ☞ ሥርዓተ ጾታን ማስረጽ እና የአካል ጉዳተኞችን ማካተት ስልጠና የወሰዱ ሰልጣኞች ቁጥር



የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች/አዲስ አበባ/ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል/መላኩ ተ.

# ሴቶችን ለማብቃት በጋራ ለመስራት የትብብር ጥሪ

የማህበረሰብ መር የተፋጠነ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፤ የአካባቢና የግል ንጽህና ፕሮጀክት (ኮዋሽ) በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ሴቶችን በማብቃት የገጠር ሴቶችንና ልጃገረዶችን የኑሮ ሁኔታ መለወጥ እንዲቻል በቅንጅትና በትብብር መስራት አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት በዘርፉ ለተሰማሩ ባለድርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች በሙሉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በቅንጅትና በትብብር ተግባራዊ ሊደረጉ ከሚችሉ ዋና ዋና ሥራዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ሴቶችንና ልጃገረዶችን የማብቃት አስፈላጊነት ግንዛቤ ለመፍጠር የሰው ሃይል፣ የገንዘብና የማቴሪያል አቅምን ማጎልበት
- ሴቶችን ለማብቃት የሚከናወኑ ተግባራት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ያማከለና በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ
- የተለያየ የመረጃ መረቦችን በመጠቀም ሴቶችንና ልጃገረዶችን በማብቃት ሥራ የተገኙ ልምዶችንና እውቀትን ማሰራጨት
- ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለማብቃት ውጤት የሚያስገኙ ስልቶችንና ተሞክሮዎችን በስፋት መጠቀም
- የገጠር ሴቶችና ልጃረገዶች ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች መፍታት

**ኮዋሽ "ሴቶችን ማብቃት ህብረተሰቡን ማብቃት ነው" የሚል መሪ ቃል ያስተጋባል፤ በውሃ፣ ንጽህናና ሃይጅን ዘርፍ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትም ይህንኑ መርህ እንዲከተሉ ጥሪ ያቀርባል፡፡**

**ኮዋሽ ለሚደረግለት ሁለገብ ድጋፍ ለኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስትና ለክልል ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ለፊንላንድ መንግስት የላቀ ምስጋና ያቀርባል፡፡**





የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ግንባታ በጤና ኬላና በትምህርት ቤት / ደብብሕ ክልል/ኦሮሚያ ክልል/ በንቲ እ.



የማህበረሰብ መር የተፋጠነ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፤

የአካባቢና የግል ንጽህና ፕሮጀክት (ኮዋሽ)

የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ፣ አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

+251 921 77 50 98

ኢሜል : arto.suominen@cmpethiopia.org

ዌብ ሳይት : WWW.cmpethiopia.org